የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፻፩
አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

33th Year No.101
Addis Ababa 8th, April 2025

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፻፺፩/፪ሺ፲፯**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ምክር ቤት እና የአደጋ ጊዜ ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ**

**ገጽ ....................................፫ሺ፱፻፶፱**

**CONTENT**

**PROCLAMALATION No. 191/2025 ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT REGULATION ON THE ESTABLISHMENT OF DISASTER RISK MANAGEMENT COUNCIL AND EMERGENCY FUND**

**Page ........................................3959**

**ደንብ ቁጥር ፻፺፩/፪ሺ፲፯**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ምክር ቤት እና የአደጋ ጊዜ ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ**

የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲን በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ በውጤታማነት ለመተግበር እንዲሁም የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን የትብብር፣ የስርጸት፣ ቅንጅታዊ አሰራርና ተጠያቂነት እንዲኖር የሚያስችል የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ምክር ቤት ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች አደጋዎች ሲከሰቱ የሚያስከትሉት የሰው፣ የንብረት ብሎም የነዋሪ መፈናቀል ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ የጉዳቱ ሰለባ የከተማዋ ነዋሪዎችን መልሶ ለማቋቋም እጅግ ከፍተኛ ሀብት የሚጠይቅ በመሆኑ፤

የአደጋ ዝግጁነትን በማረጋገጥ ለአደጋ ተጎጂዎች የአስቸኳይ ጊዜ የሰብዓዊ ዕርዳታና ድጋፍ፣ የመልሶ ግንባታ እና በዘላቂነት መልሶ ማቋቋም ሂደት የሚያስፈልግ ሀብት የማሰባሰብና የማስተዳደር የአፈጻጸም ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

**PROCLAMALATION No. 191/2025 ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT REGULATION ON THE ESTABLISHMENT OF DISASTER RISK MANAGEMENT COUNCIL AND EMERGENCY FUND**

**WHWREAS,** it has been found necessary to establish a Disaster Risk Management Council that will provide the various stakeholders with cooperation; induction; coordination and accountability as well as effectively implement the National Disaster Risk Management Policy at the Addis Ababa City level;

**WHWREAS,** it has become necessary to the victim of the damage requires extremely high resources to rehabilitate the City's residents in Addis Ababa City Government, the human, property that causes the damage of resident displacement when disasters are caused by natural and man-made causes;

**WHWREAS,** it has been found necessary to support for disaster victims by ensuring disaster readiness, restoration and resources needed through the process of sustainable rehabilitation and establish a performance procedure for the collection and administration of emergency humanitarian aid;

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፭ አንቀፅ ፺፬ መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል-አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ምክር ቤት እና የአደጋ ጊዜ ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፺፩/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም ሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"የከተማው አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"አዋጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፭ ነው፤

፬. **"ካቢኔ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ነው፤

፭. **"የከተማ ሥራ አስኪያጅ"** ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቻርተሩ አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፩ሺ፱፻፺፭ አንቀፅ ፳፬ የተመለከቱት ስልጣንና ተግባር ያሉት ሥራ አስኪያጅ ነው፤

፮. **"ኮሚሽን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ነው፤

፯. **"አደጋ"** ማለት መንስኤው የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ሆኖ የሕብረተሰቡን የዕለት ከዕለት ኑሮ በከፍተኛ ሁኔታ የሚያስተጓጉል፣ በሰው፣ በንብረት፣ በኢኮኖሚ ወይም በአካባቢ ላይ መጠነ ሰፊ ጉዳትና ተጽዕኖ የሚያስከትልና የአደጋው ተጎጂ የራሱን አቅምና ጥሪት ተጠቅሞ ለመቋቋም ከአቅሙ በላይ የሆነ ክስተት ነው፤

፰. **"የአደጋ ዝግጁነት"** ማለት አግባብነት ያለው የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ክስተትና ጉዳት ስጋቶች፣ የሚያስከትሏቸውን ተፅዕኖዎች መተንበይ፣ ምላሽ መስጠትና መቋቋም የሚያስችሉ በመንግስት፣ በባለሙያዎች፣ በተቋማትና በህብረተሰቡ ሊተገበሩ የሚችሉ ሀብቶች፣ ዕውቀቶችና አቅሞችን መፍጠርና ማደራጀት ነው፤

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 94 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No.84/2023, the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This regulation may be cited as the "Addis Ababa City Government Regulation on Establishment of Disaster Risk Management Council and Emergency Fund Regulation No. 191/2025".

### 2. Definition

In this regulation, unless the context provides otherwise:

1. "**City**" means the Addis Ababa City;
2. "**City Government**" means the Addis Ababa City Government;
3. "**Proclamation**" means the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the Power and Duties Proclamation No. 84/2023;
4. "**Cabinet**" means the Cabinet of Addis Ababa City;
5. "**Manager of the City**" means the manager with the powers and duties as indicated by Article 24 of the amended Charter Proclamation No. 361/2003 of the City Government of Addis Ababa;
6. "**Commission**" means the Fire and Disaster Risk Management Commission of Addis Ababa City Government;
7. "**Disaster**" means any dangerous natural and man-made event or condition that may occur intentionally or unintentionally and cause damage to the lives and property of the society resulting in the disruption of the normal livelihood as well as economic, social, and environmental chaos;
8. "**Disaster Readiness**" means the establishment and organization of the relevant knowledge and capabilities that enable them to prevent and respond to a potential disaster before it happens;

፱. **"ድንገተኛ አደጋ"** ማለት በቅጽበት የሚፈጸምና የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ የሆነ ክስተት ነው

፲. **"የአደጋ ጊዜ ፈንድ"** ማለት በቅድመ አደጋ ፣ በአደጋ እና በድህረ አደጋ ወቅት ለአደጋ ተጎጂዎች ድጋፍ እንዲውል በገንዘብ ወይም በአይነት ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰበ ሀብት ነው፤

፲፩.**"የአደጋ ተጎጂ"** ማለት በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ አደጋ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ጉዳት የደረሰበት ሰው ነው፤

፲፪.**"ሎጀስቲክ"** ማለት ለአደጋ መጠባበቂያ የተያዘ የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች፣ መጠለያዎች ወይም ድንኳኖች፣ አልባሳት፣ መሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች፣ የንጽህና መጠበቂያዎች፣ የቤትና መሰረተ ልማት መስሪያ ግብዓቶች እና የመሳሰሉት ናቸው፤

፲፫.**"የአስቸኳይ ጊዜ ሰብዓዊ እርዳታ"** ማለት በሰው፣ ሀብትና ንብረት ላይ አደጋ ሲደርስ ለአደጋ ተጎጅዎች ከሌላ አካል እርዳታ ካላገኙና ኑሯቸውን የመቀጠል ደረጃ ላይ መድረስ የማይችሉ መሆኑ ሲረጋገጥ ጊዜያዊ ሰብዓዊ ምላሽ መስጠት ወይም ህይወትን ለማዳን እና መሠረታዊ የኑሮ ገቢ ምንጮችን ለመጠበቅ እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ተመልሰው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግን ጨምሮ አደጋው እንደተከሰተ የአስቸኳይ ጊዜ የሰብአዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚከናወን ተግባር ነው፤

፲፬.**"የመልሶ ግንባታ"** ማለት የአደጋ ተጎጂዎች በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት የወደመባቸውን ሀብትና ንብረት አቅም በፈቀደ ልክ መልሶ በመተካት ከችግሩ ወጥተው ወደ መደበኛ ኑሯቸው እንዲመለሱ የሚደረግ ድጋፍ ነው፤

፲፭.**"በዘላቂ መልሶ ማቋቋም"** ማለት የአደጋ ተጎጂዎች ወይም ጉዳት የደረሰበት አካባቢ፣ ህዝብና የኢኮኖሚ ዘርፎች ከጉዳቱ መልሰው እንዲቋቋሙ፣ ወደተለመደው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው እንዲመለሱ እና ወደፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን መቋቋም የሚያስችላቸው አቅም እንዲገነቡ በድህረ- አደጋ ወቅት የሚወሰድና አስፈላጊ የሆነ እርምጃ ነው፤

9. **"Emergency"** means an event in which the real-time and the damage it causes is significant;

10. **"Emergency Fund"** means resources collected from a wide variety of sources, either financially or in kind, to be used in support of disaster victims during the pre-disaster, disaster and post-disaster period;

11. **"Disaster Victim"** means a person who has been injured in a natural or man-made accident directly or indirectly;

12. **"Logistic"** means food and non-food materials, shelters or tents reserved for disaster reserves, clothing, basic consumer goods, sanitation facilities, home and infrastructure workstations, and so on;

13. **"Emergency Humanitarian Assistance"** means the temporary humanitarian response to disaster victims in the event of a disaster involving people, resources, and property if they do not receive assistance from another party and are proven unable to reach the point of continuing their livelihood, including to save lives and protect basic sources of living income, as well as to ensure that essential service facilities can return and provide services, an activity that is performed to meet emergency humanitarian aids as soon as the disaster occurs;

14. **"Restoration"** means the support for disaster victims to return to their normal lives out of the crisis by restoring the resources and property they have been destroyed as a result of their damage;

15. **"Sustainable Rehabilitation"** means a step that is taken and necessary during a post-disaster to ensure that disaster victims can recover or build a capacity for the affected area, population and economic sectors to cope with the damage, return to their normal routine, and deal with future risks;

፲፮.**“ምግብ ነክ”** ማለት የብርዕ፣ የአገዳ እና የጥራጥሬ እህሎች፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ የእንስሳት ተዋጸኦ፣ አልሚ ምግብ፣ የዱቄት ወተት፣ ዱቄት፣ ፓስታ፣ ብስኩት፣ ቴምር፣ የምግብ ዘይት እና የመሳሰሉትን የታሸጉና ያልታሸጉ ምግቦችን የሚያጠቃልል ነው፤

፲፯.**“የመጠባበቂያ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ክምችት”** ማለት ለአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎት የሚውል፣ በኮሚሽኑ የማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ በመጠባበቂያነት የሚያዝ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ ክምችት ነው፤

፲፰.**“እርዳታ”** ማለት ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎችን ለመታደግ የሚያስፈልጉ እንደ መጠለያ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ፣ ውሃ፣ መድሃኒት፣ የንጽህና መጠበቂያና የመሳሰሉትን ለተጎጂዎች መስጠት ነው፤

፲፱.**"የጊዜያዊ ማቆያ ማዕከል"** ማለት በአደጋ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ወቅት በአደጋ መድረስ ምክንያት ሊጎዱ የሚችሉ አካላትን በማውጣት ለጊዜው የሚቆዩበት ቦታ ነው፤

፳.**“ፓኬጅ”** ማለት በአደጋ ጉዳት የደረሰበት ህብረተሰብ ከጉዳቱ መልሶ እንዲቋቋም የሚቀርብ አማራጭ የድጋፍ ማዕቀፍ የያዘ ሰነድ ነው፤

፳፩.**“ማህበራዊ ተጋላጭነት”** ማለት ከሥርዓተ ፆታ፣ ከዕድሜ፣ ከሥራ ዓይነት፣ ቦታ፣ የመሳሰሉት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው አካላዊ ያልሆኑ ተጋላጭነቶች ሲሆኑ የማንነት፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባሕላዊ ሁኔታዎች ያካትታሉ፤

፳፪.**“አደጋን በይፋ ማሳወቅ”** ማለት አደጋ በደረሰበት አካባቢ በሚገኝ ኃላፊነት ያለው ባለሥልጣን የአደጋው ክብደት እንዲሁም መጠን በአካባቢው አቅም በአጥጋቢ ሁኔታ መቋቋም የማይቻል እና የሌሎችን ድጋፍ የግድ የሚፈልግ መሆኑን ሲያረጋግጥ የሚሰጠው ሕጋዊ መግለጫ ነው፤

፳፫.**“መፈናቀል”** ማለት ሰዎች በአደጋ ምክንያት የመኖሪያ ቤቶቻቸውን ወይም አካባቢያቸውን ለመልቀቅና ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ የመገደድ ሂደት ነው፤

16. **"Food-Related”** means defined as a combination of silver; cane and legume grains, vegetables, fruits, animal products, nutritious food, powdered milk; flour; pasta; biscuits; dates; cooking oil, and so on, which includes canned and unpacked foods;
17. **“Reserve Food and Non-Food Stock”** means a non-food and non-food reserve that is used for emergency purposes, held as a reserve in the commission's warehouse;
18. **“Aid"** means to provide victims with food and non-food such as shelter, water, medicine sanitizer and so on, which are needed to save victim people;
19. **"Temporary Reservoir Centre"** means a place for temporary stay during an emergency early warning by removing potentially damaging components from an disaster's reach; it is also a place to stay temporarily;
20. **“Package”** means a document that contains an alternative support framework that provides for a society affected by a disaster to be able to cope back from the damage;
21. **“Social Vulnerability”** means non-physical vulnerabilities relevant to gender, age, type of work, place, so on, while identity, economic, political, cultural factors include;
22. **“Publicizing a Disaster”** means an appropriate briefing given by the relevant authority when a local authority at the place where a disaster happened confirms the severity of the disaster and it could not be properly handled by the local community and needs the support of others;
23. **“Displacement”** means the process of people being forced to vacate their housing or surrounding areas and move elsewhere due to a disaster;

፳፬."**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. **<u>የፆታ አገላለጽ</u>**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

፬. **<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በአደጋ ስጋት ሥራ አመራር እና በሚከሰት አደጋ የተጎዱ ሰዎች የአስቸኳይ ጊዜ ሰብዓዊ ዕርዳታ፣ የመልሶ ግንባታና በዘላቂነት መልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ምክር ቤት መቋቋም፣ ተግባርና እና ኃላፊነት</u>**

፭. **<u>መቋቋም</u>**

፩. በአደጋ ሥጋት ቅነሳ፣ በአደጋ ምላሽ፣ በአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ በመልሶ ግንባታ፣ በዘላቂነት መልሶ ማቋቋም እና በአደጋ ዝግጁነት ፈንድ አሰባሰብ የአጋር አካላት ተሳትፎን ለማጠናከር የሚያግዝ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. የምክር ቤቱ ተጠሪነት ለከንቲባ ይሆናል፤

፫. ኮሚሽኑ የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፡፡

፮. **<u>ዓላማ</u>**

የምክር ቤቱ ዓላማ በአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር በቅድመ አደጋ ጊዜ እና በድህረ አደጋ ወቅቶች በሚሰጡ አገልግሎቶች ዙሪያ የሚታዩ ማነቆዎችን ለመፍታት፣ አሰራሩን ለማዘመን እና አገልግሎቶቹ ለከተማው አጠቃላይ ዘላቂ ልማት ቀጣይነት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ በሚያግዙ ሀሳቦች ላይ ምክክር ማድረግ እና አቅጣጫ ማስቀመጥ ይሆናል፡፡

፯. **<u>የምክር ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል:-

24. "**Person**" means any physical or juridical person.

3. **<u>Gender Expression</u>**

In this Regulation, any expression in the masculine gender includes the feminine.

4. **<u>Scope of Application</u>**

This Regulation shall be applicable on the emergency humanitarian aid, restoration and sustainably rehabilitate activities in Addis Ababa City Government by disaster risk management and people affected by the disaster.

**<u>PART TWO</u>**

**<u>ESTABLISHMENT, DUTY AND RESPONSIBILITY OF THE DISASTER RISK MANAGEMENT COUNCIL</u>**

5. **<u>Establishment</u>**

1. A Disaster Risk Management Council was established (hereafter referred to as "the **Council**",) under this Regulation to help strengthen the participation of partners in disaster risk reduction, disaster response, emergency aid, restoration, sustainable rehabilitation and disaster readiness fund collection;
2. The Council's accountability will be to the Mayor;
3. The Commission serves as the Council's Office.

6. **<u>Objective</u>**

The objective of the Council will be to address visible bottlenecks around services provided by Disaster Risk Management in the pre-disaster and post-disaster periods, to update its operations and to consult and orient its services on proposals that will help increase its contribution to the continuation of the overall sustainable development of the City.

7. **<u>Duty and Responsibility of the Council</u>**

The Council will have the following duty and responsibility:

፩. በአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ አፈጻጸም ላይ አጠቃላይ አመራር ይሰጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አቅጣጫ ይሰጣል፤

፪. ኮሚሽኑ በአደጋ ሥጋት ቅነሳ ፣ በአደጋ ምላሽ ፣ በአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ በመልሶ ግንባታ፣ በዘላቂነት መልሶ ማቋቋም እና በአደጋ ዝግጁነት ፈንድ አሰባሰብ ዕቅድና አተገባበር ላይ ውይይት ያደርጋል፤ አቅጣጫዎችን ይሰጣል፤

፫. የአደጋ ስጋት ምላሽ መጠባበቂያ ፈንድ ለማሳደግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፤ የፈንዱን አሰባሰብና፤ የድጋፍ አሰጣጥ መርሆዎችን እንዲሁም ከአጠቃቀም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡

፬. የአደጋ ተጎጂዎችን ለመደገፍና ለማቋቋም የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችና ፓኬጆች ኮሚሽኑ የሚያካሂደውን የሀብት አሰባሰብና አስተዳደር ዕቅድና ትግበራ ላይ ውይይት ያደርጋል፤ የመደገፍና የማማከር ሥራ ይሰራል፤ የአተገባበር አቅጣጫ ይሰጣል፤

፭. የከተማ አስተዳደሩን የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር አገልግሎት ተደራሽና ውጤታማ እንዲሆን የሁሉንም ተዋናዮች አቅም ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የሚያስችል አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ አፈጻጸሙን ይገመግማል፤

፮. አደጋ መከሰት በይፋ መገለጹን ተከትሎም ሆነ ለከተማው አደጋ ስጋት የሚያስፈልጉ ሀብቶች እንዲሰበሰቡ ድጋፍ ያደርጋል፣

፯. የአደጋውን መጠን እና ውስብስብነት መሰረት በማድረግ የፌደራል መንግስቱ ድጋፍ የሚሻ አደጋ መከሰቱን ወይም የተከሰተው አደጋ መወገዱን ይፋ ያደርጋል፤

፰. ለምላሽ ሥራ ተጨማሪ ሀብት የሚያስፈልግ ሲሆን ከከተማው አስተዳደር እንዲመደብ ወይም እንደ አስፈሊጊነቱም ከሌሎች አካላት ድጋፍ እንዲደረግ ይጠይቃል፤

፱. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ስለተመደበው በጀት አጠቃቀም ይከታተላል፤ ሥራ ላይ ያልዋለ ሀብት ቢኖር ከአስተዳደሩ የሚመደበው በጀት የተመጣጠነ እንዲሆን ያደርጋል፤

1. It provides comprehensive leadership on policy and strategy performance in disaster risk management, monitors and evaluates its implementation, and provides direction when necessary;
2. The Commission also conducts discussions on the planning and implementation of disaster risk reduction, disaster response, emergency aid, restoration, sustainable rehabilitation and disaster readiness fund collection; it provides directions;
3. The Disaster Risk Response Reserve Fund devises strategies to enhance; it provides the fund's collection; it makes decisions on support principles as well as use-related issues, and monitors its performance;
4. Projects and packages implemented to support and rehabilitate disaster victims include discussions on the planning and implementation of the resource collection and administer that the commission conducts; it does support and consultancy work; it provides an implementation direction;
5. It sets the direction for the effective use of the capabilities of all actors in order to make the City Administration's Disaster Risk Management Service negotiable and effective; it evaluates its performance;
6. It supports the collection of resources needed for the risk of urban disaster, both following the official declaration of a disaster;
7. Based on the magnitude and complexity of the disaster, the Federal Government will announce that a disaster requiring support has occurred or that the resulting disaster has been removed;
8. More resources are needed for response work and it requires that they be allocated from the City Government or, depending on the threat, support from other parties;
9. Under Sub Article (1) of Article 14 of this Regulation, it monitors the use of the allocated budget; if there is a resource in force, it will ensure that the budget allocated from the administration is balanced;

፲. የተሰበሰበውን ሀብት በአግባቡ ህግና ሥርዓት ተከትሎ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ የአሰራር ክፍተት ሲኖር ማስተካከያ ሀሳብ ያቀርባል፤

፲፩. የፈንዱ አላማ በሚመለከተው አካል ሁሉ እንዲታወቅና ድጋፍ እንዲያገኝ ያደርጋል፤

፲፪. በአደጋ ሥጋት ቅነሳ፣ በአደጋ ምላሽ፣ በአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ በመልሶ ግንባታ፣ በዘላቂነት መልሶ ማቋቋም እና በአደጋ ዝግጁነት ፈንድ አሰባሰብ ተዋንያንና ባለድርሻ አካላት እውቅና እና ማበረታቻ የሚሰጥበት ሥርዓት እንዲዘረጋና ተግባራዊ እንዲሆን ይመክራል፤ አቅጣጫ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

፰. **የምክር ቤቱ አባላት**

፩. ምክር ቤቱ በከንቲባው የሚሰየሙ፡-

ሀ) አግባብ ያላቸው በየደረጃው ካሉ የአስተዳደሩ አስፈጻሚ ተቋማት ኃላፊዎች፤

ለ) የሀይማኖት ተቋማት፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የሚዲያ አካላት፤

ሐ) ከአዲስ አበባ ከተማ የንግድ ዘርፍ ማህራት፤ እና

መ)የሌሎች አግባብ ያላቸው አካላት ተወካዮችን፤ በአባልነት የሚይዝ ይሆናል፡፡

፪. ምክር ቤቱ በከንቲባው ሰብሳቢነት ይመራል፤ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ጸሐፊ ይሆናል፤

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የአስተዳደሩ የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም ሙያዊ አስተያየት እንዲያቀርቡ የሚጋበዙ ባለሙያዎች በስብሰባው እንዲሳተፉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፱. **የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**

፩. ምክር ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤

፪. ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፤

10. It monitors the appropriately followed by law and order of the collected resources and proposes adjustment when there is a procedural loophole;
11. The objective of the fund is to be recognized and supported by every party concerned;
12. It recommends the development and implementation of a procedure in which actors and stakeholders can be recognized and encouraged through disaster risk reduction, disaster response, emergency aid, restoration, sustainable rehabilitation and disaster readiness fund collection; it provides direction and monitors its performance.

8. **Members of the Council**

1. The Council is designated by the Mayor as:
   a) Appropriate to the Heads of the Executive Institutions of the Administration at all levels;
   b) Religious Institutions, Civil Society, Media Bodies;
   c) The Commercial Sector of Addis Ababa; and
   d) Shall consist of Representatives of other appropriate Bodies; and shall hold them as Members.
2. The Council is chaired by the Mayor, who becomes the Commission's Commissioner is Secretary;
3. While the Council finds it to be necessary, subject to the provision of a Sub Article (1) of this Article, it may also result in other officials of the administration, as well as professionals invited to submit professional opinions, participating in the meeting.

9. **Meetings of the Council**

1. The Council holds regular meetings twice a year, however, when it turns out to be necessary, it may meet at any time at the convener's call;
2. If more than half of the Council members attend a meeting, it becomes a quorum;

፫. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የውስጥ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲. <u>የኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

ኮሚሽኑ በአዋጅ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ሲባል የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩. የመጠባበቂያ ፈንዱን ይሰበስባል፣ ያስተዳድራል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፪. የፈንዱ አላማ እንዲታወቅ ያደርጋል፤

፫. የፈንዱ ገቢ የሚያድግበትን እቅድ ያወጣል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፬. ለአገልግሎት የማይውሉ ንብረቶችን በከተማው አስተዳደር ግዥና ንብረት አስተዳደር ሕግ መሠረት ከሚመለከተው የአስተዳደሩ አስፈጻሚ ተቋም ጋር በመቀናጀት ያስወግዳል፤ ንብረቱ በሽያጭ የሚወገድ ከሆነ ገንዘቡን በፈንዱ አካውንት ገቢ ያደርጋል፤

፭. ለአደጋ መጠባበቂያ ሀብት አሰባሰብ ያስተባብራል፤ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት አብሮ ይሰራል፤

፮. ከኮሚሽኑ ዕቅድ ወይም አቅም በላይ የሆነ አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ ለከተማ አስተዳደሩ ያሳውቃል፤

፯. ለፕሮጀክቱ የተመደበውን በጀት በከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስ ሕግ መሰረት ለከተማው የአደጋ መልሶ ግንባታና መልሶ መቋቋም እንዲውል ያደርጋል፤

፰. ማንኛውም ጉዳት የደረሰበት ቤተሰብ ወይም ግለሰብ በስታንዳርዱ መሰረት እርዳታ እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

**<u>ክፍል ሦስት</u>**

**<u>የአደጋ ጊዜ ፈንድ መቋቋም እና አስተዳደር</u>**

**፲፩.<u>ስለ አደጋ ጊዜ ፈንድ መቋቋም</u>**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአደጋ ጊዜ ፈንድ (ከዚህ በኋላ "ፈንድ" እየተባለ የሚጠራ) በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮ በኮሚሽኑ ስም በሚከፍተው ልዩ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ተቀማጭ እንዲሆን በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

3. Notwithstanding of this Article, the Council may adopt its own internal rules of meeting procedure.

**10. <u>Duty and Responsibility of the Commission</u>**

The Commission shall have the following duty and responsibility for the implimentation of this Regulation, subject to the powers and duties conferred by Proclamation:

1. It collects, administers, makes the reserve fund operational, monitors, controls and administers its performance;
2. The objective of the fund makes it known;
3. It sets out a plan in which the fund's revenue will grow, putting it into operation;
4. It removes non-useable assets in coordination with the relevant executive institution of the administration under the City Government Procurement and Property Administration Proclamation; if the property is to be disposed of by sale, it will monetize the money through the fund's account;
5. It coordinates resource collection for disaster reserves and works in coordination with various stakeholders;
6. It notifies the City Government in the event of a disaster that exceeds the Commission's plan or capacity;
7. It will make the budget allocated for the project available for the City's disaster restoration and rehabilitation under the City Government Finance Proclamation;
8. Any victim family or individual will be provided with aid according to the stand.

**<u>PART THREE</u>**

**<u>EMERGENCY FUND ESTABLISHMENT AND ADMINISTRATION</u>**

**11. <u>Establishment of the Emergency Fund</u>**

1. The Addis Ababa City Government Emergency Fund (hereafter referred to as "the **Fund**") was established under this Regulation to be a deposit in a special bank account that is opened by the City Government's Finance Bureau on behalf of the Commission;

፪. ፈንዱ በኮሚሽኑ የሚተዳደር ይሆናል፡፡

፲፪. **የፈንድ ዓላማ**

፩. አደጋ መከሰትን ተከትሎ ወይም በከተማው የአደጋ ስጋት መነሻ ለድህረ አደጋ ምላሽ አገልግሎቶች እንደ አስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ፣ መልሶ ግንባታና በዘላቂነት መልሶ ለማቋቋም የሚያስፈልጉ ሀብቶችን ማሰባሰብና ዝግጁ ማድረግ፤

፪. የአደጋ ተጎጂዎችን የአስቸኳይ ጊዜ ሰብዓዊ ዕርዳታ፣ የመልሶ ግንባታና በዘላቂነት መልሶ የማቋቋም ተግባራት፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነትን መሠረት ያደረገ የዜጎች ከአደጋ የማገገም መብትና ተጠቃሚነት የማረጋገጥ አሰራር መዘርጋት፤

፫. በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የመጠባበቂያ ዕቅድ መነሻ በድህረ አደጋ ወቅት ከአደጋ ጉዳት ለማገገም፣ የአስቸኳይ ጊዜ ሰብዓዊ ዕርዳታ፣ መልሶ ግንባታና በዘላቂነት መልሶ ማቋቋም ፍላጎቶች የሚውል በራስ አቅም የሰብዓዊ ድጋፍ ዝግጁነትና የአደጋ መቋቋም አቅምን ማረጋገጥ፤

፬. በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በድህረ አደጋ ወቅት የሥነ-ልቦና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የአደጋ ተጎጂዎች አደጋን የመቋቋም አቅም መፍጠር፡፡

፲፫. **የፈንዱ ምንጭ**

ፈንዱ በገንዘብ፣ በዓይነት ወይንም በቁሳቁስ፣ በአቅም ግንባታ፣ የቴክኒካል ድጋፍ ሆኖ ከሚከተሉት የሀብት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡-

፩. በየዓመቱ ከከተማው አስተዳደር የሚመደብ ተዘዋዋሪ የአደጋ ዝግጁነት መጠባበቂያ በጀት፤

፪. ከአጋር አካላት፣ ከሀገር ውስጥና ውጭ የሚገኙ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ከአባላት ከሚገኝ ድጋፍ፤ እርዳታና ስጦታ፤

፫. ከከተማ አስተዳደሩ ማህበራዊ ትረስት ፈንድ ቋት፡፡

፲፬. **የፈንዱ ገቢ አሰባሰብ**

ፈንዱ ገቢውን ከሚመለከታቸው አካላት በሚከተለው መጠን ይሰበስባል፡-

2. The fund will be administered by the Commission.

12. **Objective of the Fund**

1. Following a disaster, or at the origin of the City's risk of disaster, for post-disaster response services such as emergency aid, restoration, and the mobilization and readiness of resources needed for sustainable rehabilitation;
2. The development of emergency humanitarian aid, restoration and sustainable rehabilitation activities for disaster victims, and a procedure for ensuring the right and use of citizens' recovery from disasters based on responsibility and accountability;
3. The premise of the reserve plan for natural and man-made disasters is to ensure self-capable human support readiness and disaster resilience for recovery from disaster damage during the post-disaster, emergency humanitarian aid, restoration and sustainable rehabilitation needs;
4. Creating disaster resistance capacity to disaster victims who need psychological support in the aftermath of natural and man-made disasters:

13. **Source of the Fund**

The fund will be made up of the following sources of treasure, whether in money, type or material, capacity building, as technical support:

1. A revolving disaster readiness waiting budget, allocated annually from the City Government;
2. From support from partners, NGOs and charities within and outside the country and from members; grants and gifts;
3. From the City Government's Social Trust Fund Buffer.

14. **Fund Revenue Collection**

The fund collects its income from the relevant entity in the following amount:

፩. ከከተማ አስተዳደሩ ባለበጀት መሥሪያ ቤት ሥራ ማስኪያጃ በጀት ፩% (አንድ በመቶ)፣
፪. ከከተማ አስተዳደሩ መንግሥት ሠራተኛ እና ተሿሚ በወር ከተጣራ ደመዎዝ ዜሮ ነጥብ ፭% (ዜሮ ነጥብ አምስት በመቶ)፣
፫. ከከተማ አስተዳደሩ የመንግሥት ልማት ድርጅት የሥራ ማስኪያጃ በጀት ፪% (ሁለት በመቶ)፣
፬. ከንግዱ ማህበረሰብ በግብር አሰባሰብ ወቅት ከግብር ጋር ተሰልቶ የሚከፈል፦
   ሀ) ደረጃ “ሀ” ግብር ከፋይ በወር ብር ፪፻ (ሁለት መቶ ብር)፣
   ለ) ደረጃ “ለ” ግብር ከፋይ በወር ብር ፩፻(አንድ መቶ ብር)፣
   ሐ) ደረጃ “ሐ” ግብር ከፋይ በወር ብር ፶ ሃምሳ ብር)፣
፭. የከተማ ነዋሪ በዓመት ብር ፷ (ስድሳ ብር) በወር ብር ፭ (አምስት ብር) በውሃ ማስከፈያ ቢል ጋር ተጨምሮ መክፈል፤
፮. ከቋሚ ንብረት ግዥና ሽያጭ ወቅት ከሻጭና ከገዥ ከሽያጭ ዋጋ ላይ ዜሮ ነጥብ ፩% (ዜሮ ነጥብ አንድ በመቶ)፣
፯. በከተማው ውስጥ ካሉ ኃይማኖት ተቋማት በየዓመቱ በአጥቢያ ብር ፲፪ ሺ. (አስራ ሁለት ሺህ ብር)፤
፰. የሲቪክ ማህበራት ፈቃድ ሲያወጡና ሲያድሱ በዓመት ብር ፭ሺ. (አምስት ሺህ ብር)፡፡

**፲፭. ስለሀብት ማሰባሰብ**

፩. ኮሚሽኑ ከከተማ አስተዳደሩ ዓመታዊ በጀት እና ከማህበራዊ ትረስት ፈንድ የተመደበለት ሀብት ይጠይቃል፤ ይሰበስባል፤
፪. ኮሚሽኑ ከአጋር አካላት፣ ከሀገር ውስጥና ውጭ የሚገኙ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና በጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት ሀሳብ በማዘጋጀት ሀብት ይጠይቃል፤ ይሰበስባል፤
፫. ኮሚሽኑ ከአጋር አካላት እና ከለጋሽ አካላት የሚሰጡ ድጋፍና ስጦታዎችን ይቀበላል፤

1. 1% (one percent) of the City Government's budget office operation budget;
2. 0.5% (zero point five percent) of the net salary per month from the civil servant and appointee of the city government;
3. 2% (two percent) of the City Government's Public Enterprise's operation budget;
4. From the Commercial Community, through tax collection;
   a) Level "A" taxpayer 200.00 (two hundred) Birr per month;
   b) Level "B" taxpayer 100.00 (one hundred) Birr per month;
   c) Level "C" taxpayer 50.00 (fifty) Birr per month;
5. Urban resident paid 60.00 (sixty) Birr per year, 5.00 (five) Birr per month with the addition of a water bill for charging;
6. 0.1% (zero point, one percent) of the sale price of a seller and buyer during the purchase and sale of a fixed asset;
7. 12,000.00 (twelve thousand) Birr annually in the neighborhood from Religious Institutions in the City;
8. When the civil society groups issue and renew licenses, they have a yearly 5,000.00 (five thousand) Birr.

**15. Resource Collection**

1. The Commission requires an annual budget from the City Government and a allocated amount of resources from the Social Trust Fund, which it collects;
2. The Commission solicits and collects resources from partners, NGOs and charities within and outside the country through the development of a project proposal;
3. The Commission receives support and gifts from the partners and donors;

፬. ከመንግሥት ሠራተኞች እና ተሿሚዎች የሚሰበሰበውን ወርሃዊ ክፍያ በየአስተዳደሩ አስፈጻሚ ተቋማት ወይም የልማት ድርጅቶች ፋይናንስ የሥራ ክፍል ወይም በፋይናስ ቢሮ በኩል እየተሰበሰበ ወደ ፈንዱ ቋት ገቢ ይደረጋል፤

፭. ከንግዱ ማህበረሰብ የሚሰበሰበው ክፍያ በግብር ወቅት በገቢዎች ቢሮ በኩል ተሰብስቦ ወደ ፈንዱ ቋት ገቢ እንዲሆን ይደረጋል፤

፮. ከከተማው ነዋሪ በየወሩ ከውሃ መክፈያ ቢል ጋር በማካተት በውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን እየተሰበሰበ ወደ ፈንዱ ቋት እንዲገባ ይደረጋል፤

፯. ከቋሚ ንብረት ሽያጭና ግዥ የሚሰበሰበው ገንዘብ በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ወይም የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አማካኝነት በየወሩ እየተሰበሰበ ወደ ፈንዱ ቋት ገቢ ይደረጋል፤

፰. በከተማው ያሉ የኃይማት ተቋማት ዓመታዊ ክፍያ በኮሚሽኑ ልዩ የባንክ ሂሳብ በኩል ወደ ፈንዱ ቋት ገቢ እንዲገባ ያደርጋሉ፤ ኮሚሽኑ ለተከፈለው ክፍያ ደረሰኝ ለከፋዩ የኃይማኖት ተቋም አጥቢያ ይሰጣል፤

፱. በከተማው ያሉ ሲቪክ ማህበራት ዓመታዊ ክፍያ በየዓመቱ በፌደራል ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን እየተሰበሰበ ለፈንዱ በተከፈተው የኮሚሽኑ ልዩ የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደርጋል፤ ኮሚሽኑ ለተከፈለው ክፍያ ደረሰኝ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ይሰጣል፤

፲. በዚህ አንቀጽ መሠረት ከማንኛውም እረጂ ድርጅት የሚገኝ ቁሳቁስ፣ ምግብ፣ መድሃኒቶችና ሌሎች ግብዓቶች የመወገጃ ጊዜያቸው ያላለፈና ፮ ወርና ከዚያ በላይ የቀረው ሆኖ ተገቢውን ስታንዳርድ እና የጥራት ደረጃ የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

## ፲፮. <u>ስለ ፈንድ አስተዳደር</u>

፩. በአይነት የሚሰበሰበው ሀብትና ንብረት በኮሚሽኑ ልዩ መጋዝን ውስጥ የሚከማች ይሆናል፤

4. The monthly payments collected from government employees and appointees are collected through the finance work department of each Administration's Executive Institutions or Civil Society, or through the Bureau of Finance, and then proceeds to the fund's crest.

5. The fees collected from the commercial community are collected through the Revenue Bureau during the tax season and are then put into the fund's buffer to be monetized;

6. It is incorporated monthly from the City's resident with a water payment bill, which is collected by the Water and Sewerage Authority to enter the fund's buffer zone;

7. Funds rose from the sale and purchase of permanent property are raised monthly through the Bureau of Land Development and Administration or the Land Holdings Registration and Information Agency and are then raised to the fund's buffer;

8. The Religious institutions in the city make annual payments through the commission's special bank account into the fund's buffer income; the commission gives receipts for the payments to the neighborhood Religious Institutions;

9. civic societies in the city make annual payments annually, collected by the Federal Civil Society Organizations Authority, through the Commission's special bank account opened to the fund; the Commission provides Authority to Civil Society Organizations with receipts for the payments paid.

10. According to this Article, the material, food, medicines and other resources from any donating organization must be those that meet the appropriate standard and quality standards, with no expiry period and 6 months or more remaining.

## 16. **<u>Fund Administration</u>**

1. The treasure and property collected in kind would be stored in the Commission's special warehouse;

፪. ፈንዱ በሥራ ላይ የሚውለው በከተማው አስተዳደር ፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሰረት ይሆናል፤

፫. ለመጠባበቂያ የሚሆን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ግብዓቶች ግዥ የሚፈጸመው በዋና መሥሪያ ቤቱ ይሆናል፤

፬. በአደጋ ዝግጁነት ፈንድ መጠባበቂያ የተያዘ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ግብዓቶች በአስተዳደሩ የግዥና ንብረት ሕግ መሠረት ስርጭቱ በዋና መስያ ቤቱ እና በቅርጫፍ ጽህፈት ቤቶቹ የሚከናወን ይሆናል፤

፭. ለአደጋ ዝግጁነት ፈንድ የሚሰበሰበው ሀብትና ንብረት በበጀት ዓመቱ ማብቂያ ፈሰስ ወይም ገቢ የማይደረግ ሆኖ በሪቮልቪንግ የሚቀጥል ይሆናል፤

፮. ኮሚሽኑ በከተማው በየደረጃው በስጦታና በድጋፍ ከተለያዩ ምንጮች ተሰብስበው በየመጋዘኖቹ ተከማችተው በመቆየት ሊበላሹ የሚችሉትን ወይም አገልግሎት መስጠት የማይችሉትን ንብረቶች በግዥና ንብረት አስተዳደር ሕግ መሰረት ተሸጦ በፈንዱ አካውንት ወይም የሂሳብ ቁጥር ገቢ ይደረጋል ወይም እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

**፲፯. ስለ-ድህረ አደጋ አገልግሎቶች**

የድህረ አደጋ አገልግሎቶች የሚከተሉት ይሆናሉ ፡-

፩. ለአስቸኳይ ጊዜ ሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦት ምላሽ ሥራ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆነ ቁሳቁስ በመጠባበቂያነት መያዝ፣ ማደራጀት፣ ማስተዳደር፣ ማሰራጨት፤

፪. የአሰቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ከአደጋ በኋላ የአደጋ ተጎጂዎች ወደ ነበሩበት መደበኛ ኑሮ እንዲመለሱ የሚደረግ የመልሶ ግንባታ ድጋፍ አገልግሎት፤ እና

፫. የአደጋ ተጎጂ በዘላቂነት መልሶ ማቋቋም የሚያስፈልግ መሆኑ ሲረጋገጥ የሚደረግ ድጋፍን ያጠቃልላል፡፡

**፲፰. የአስቸኳይ ጊዜ ሰብዓዊ ዕርዳታ ዓይነት**

፩. የዕለት ደራሽ ድጋፍ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች፤

2. The fund will be put into effect under the City Government Finance Administration Proclamation;

3. Procurement of food and non-food resources for the reserve will be carried out by the Head Office, which will be located at the base of the reserve;

4. Food and non-food resources held by the disaster readiness fund reserve will be procured by virtue of procurement laws at head office and branch offices.

5. Resources and property collected by the disaster readiness fund will be liquidated or non-revenue able by the end of the fiscal year and will continue through revolving;

6. The Commission is collected by the City in every sort of gift and support from separate sources, stored at the warehouses, and the assets that can or cannot be serviced, are sold under the Procurement and Property Administration Proclamation, and are earned or disposed of by the fund's account or account number;

**17. Post-Disaster Services**

Post-disaster services will be as follows:

1. Holding, organizing, managing, distributing food and non-food material as reserves for use in response to emergency humanitarian aid supplies;

2. Emergency aid is a restoration support service for the return of disaster victims to normal life after disasters; and

3. It includes support when it is proven that disaster restoration is needed in perpetuity.

**18. Types of Emergency Humanitarian Aid**

1. Daily convergent support food and non-food materials;

፪. የሥነ-ልቦና ድጋፍና፤

፫. የማቆያ ማዕከል ወይም ጊዜያዊ መጠለያ አገልግሎት ወጪዎችን የሚያጠቃልሉ ናቸው፡፡

**፲፱. የመልሶ ግንባታ ድጋፍ ዓይነት**

፩. በአደጋው በወደመው ንብረት ልክ መልሶ መገንባት፤

፪. መሠረታዊ የቤት ቁሳቁስ ማሟላት ወይም መጠገን፡፡

**፳. በዘላቂነት መልሶ ማቋቋም ዓይነት**

፩. በአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ የተጀመረውን መሠረታዊ ፍላጎት በዘላቂነት ማሟላት፤

፪. በዘላቂነት ለማቋቋም ፕሮጀክትና ፓኬጅ ትግበራ፤

፫. መሠረተ ልማት ማሟላት፡፡

## ክፍል አራት
## ስለአደጋ ተጎጂዎች ልየታ እና ግዴታ

**፳፩. ስለአደጋ ተጎጂዎች ልየታ**

በአደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን እና ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን ከዚህ በታች በተቀመጠው አሰራር መሠረት መለየት፡-

፩. የአደጋ ተጎጂዎችን መረጃ በመጠናቀሪያ ቅጽ መመዝገብ፣ መተንተን እና አመላካች መረጃ ማውጣት፤

፪. ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ ተቋማት እና የህዝብ አደረጃጀት ጋር በመተባበር ተጎጂዎቹ ስለሚቋቋሙበትና ድጋፍ ስለሚያገኙበት ሁኔታ የፍላጎት ዳሰሳ ማድረግ፤

፫. የተሰበሰቡት መረጃዎች በተጐጂዎችና በአካባቢው ነዋሪዎች እንዲተችና እንዲረጋገጥ ይፋ መደረግ ይኖርበታል፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የተደራጀው መረጃ አደጋው በተፈጠረበት ወይም ለአደጋ ሥጋት ተጋላጭ የሆኑ ነዋሪዎች በሚገኙበት ወረዳ የወረዳው አስተዳደር ስለትክክለኝነቱ በደብዳቤ አረጋግጦ ለኮሚሽኑ መላክ ይኖርበታል፤

፭. ከወረዳው የተሰበሰበው መረጃ ወደ ዳታ ቤዝ ከመግባቱ በፊት ኮሚሽኑ ከሰበሰበው መረጃ ጋር ማነጻጸርና ማናበብ ይኖርበታል፡፡

2. Psychological support; and

3. They include the costs of a reservoir center or temporary shelter service.

19. **Type of Restoration Support**

1. Just rebuilding with the property destroyed in the disaster;

2. Fundamental home material fulfillment or repair.

20. **Types of Sustainable Restoration**

1. To sustainably meet the basic need initiated by emergency support;

2. Project and package implementation to establish sustainability;

3. Infrastructure fulfillment.

## PART FOUR
## IDENTIFICATION OF DISASTER VICTIMS AND OBLIGATION

21. **Identification of Disaster Victims**

Identification of victim and vulnerable to victim as per the procedure set out below:

1. Registering, analyzing, and indexing information of disaster victims in a compilation form;

2. In conjunction with the relevant executive institutions and public organization, conducting a demand survey about the situation in which the victims are being set up and receiving support;

3. The information gathered will need to be made public to be criticized and verified by the victims and locals;

4. According to Sub Articles (1) and (2) of this Article, the organized information is that in the Woreda where the disaster occurred or where the residents at risk were located, the Woreda Administration would have to confirm the imprecision in a letter and send it to the Commission;

5. Before the data collected from the Woreda can be entered into the data base, the Commission will have to compare and proof read it along with the data it collected.

፳፪. **የመረጃ አደረጃጀትና አያያዝ**

፩. የተለየ የአደጋ ተጎጂን መረጃ፣ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል፣ ፓኬጅ፣ የንብረት ውድመት ትንተና፣ የክፍያ፣ የወጪ ማዘዣ፣ የስርጭት ቅፆች እና ሌሎች ሰነዶች ሃርድ ኮፒዎች ስካን ተደርገው በሶፍት ኮፒ መረጃው እንዲደራጅ ይደረጋል፤

፪. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተደራጁ መረጃዎችን ወደ ዳታ ቤዝ ያስገባል፤ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፤

፫. የመረጃውን ደህንነት ለመጠበቅ የመጠባበቂያ መረጃ ወይም ባክ አፕ ይይዛል፡፡

፳፫. **የአደጋ ተጎጂዎች ግዴታ**

፩. ኮሚሽኑ የአደጋ ተጎጂዎችን በሚለይበት ጊዜ ማንኛውም ተጎጂ የሚጠየቀውን ትክክለኛ መረጃ ማቅረብ አለበት፤

፪. የአደጋ ተጎጂው ማንኛውንም እርዳታ ወይም ድጋፍ ሲቀበል ስለመቀበሉ በፊርማ ማረጋገጥ አለበት፤

፫. ለአደጋ ተጎጂው የተሰጠውን ድጋፍ ወይም እርዳታ ለታለመለት ዓላማ ማዋል አለበት፡፡

**ክፍል አምስት**

**የአደጋ ጊዜ ፈንድ አጠቃቀም ሥርዓት**

፳፬. **የአደጋ ጊዜ ፈንድ የተጠቃሚነት መስፈርት**

፩. የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ፣ መልሶ ግንባታና በዘላቂነት መልሶ መቋቋም ፍላጎት ከሚመለከተው የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳ አስተዳደር እና ከተጎጂ መቅረብ አለበት፤

፪. በፈንዱ ሊሸፈኑ የሚችሉ የተለያዩ ወጪዎች በመጀመሪያ በኮሚሽኑ ባለሙያ ፣ ከክፍለ ከተማ ወይም ከወረዳ አስተዳደር ጉዳዩ ከሚመለከተው አስፈጻሚ ተቋም እና በአደጋ ተጎጂዎች ተወካይ ተጠንቶ ለኮሚሽኑ ቀርቦ በሚጸድቀው መሰረት መሆን አለበት፤

፫. በመደበኛ እርዳታ የታቀፉና ያልተቀፉ የአደጋ ተጎጂዎች እና እርዳታ ስለመድረሱና አለመድረሱን በየደረጃው ባለው የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳ አስተዳደር ባለሙያዎች ተጣርቶ መቅረብ አለበት፤

22. **Information Organization and Handling**

1. Separate incident victim data, project proposal, package, asset destruction analysis, payment, cost order, distribution forms, and other documents are hard copies scans and are arranged by soft copy for the data to be organized;

2. According to this Article, it inserts organized data into a data base to be used;

3. It contains backup information or back-up to keep the data safe.

23. **Obligation of Disaster Victims**

1. The Victim must provide the correct information when asked by the commission while engaged in asserttaining victims of victim;

2. The casualty of a disaster must prove by signature that he has received any aid or support while receiving it;

3. It must use the support or assistance given to the disaster victim for its intended objective.

**PART FIVE**

**EMERGENCY FUND USE PROCEDURE**

24. **Emergency Fund Beneficiary Criteria**

1. The need for emergency aid, restoration and sustainable rehabilitation must be addressed from the relevant Sub City or Woreda Administration and the victim;

2. The various costs that can be covered by the fund must first be studied by the Commission expert, the Sub City or Woreda Administration representative from the relevant executive institution and the disaster victims representative, and submitted to the Commission has approved;

3. Disaster victims, who are covered with regular aid, and whether or not aid is received, must be screened and delivered by the respective Sub City or Woreda Administration experts;

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ መሠረት በወቅቱ ተጠንቶ በኮሚሽኑ ያልጸደቀ ወይም እውቅና ያላገኘ ማንኛውም እርዳታ ከፈንድ ሊሸፈን አይችልም፤

፭. ከተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ውጪ በከንቲባ ካልተፈቀደ በቀር ለአደጋ መጠባበቂያ የተያዘ ሀብት ለሌላ ድጋፍ ሊውል አይችልም፡፡

፳፭. **የአደጋ ጊዜ ፈንድ አጠቃቀም**

፩. የፈንዱ ገንዘብ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ተጎጂ ለሆኑ ሰዎች ለአስቸኳይ ጊዜ ሰብዓዊ ድጋፍ ፣ ለመልሶ ግንባታ እና በዘላቂነት መልሶ ለማቋቋም የሚውል ይሆናል፤

፪. የአደጋ ጊዜ ፈንድ ጥቅም ላይ የሚውለው በኮሚሽኑ በሚዘጋጀው የፓኬጅና ፕሮጀክት ፕሮፖዛል መሰረት ይሆናል፤

፫. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በከተማ አስተዳደሩ ውሳኔ መሰረት ለሚመለከተው የፌደራል አስፈጻሚ ተቋም ወይም ለክልሎች ድጋፍ ሊደረግ ይችላል፤

፬. በፈንዱ እርዳታ ሊሸፈኑ የሚችሉት በኮሚሽኑ እንደ አደጋው መጠን ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ይሆናል፤

፭. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ ቢኖርም በከንቲባ ሲወሰን ከፈንዱ በገንዘብ ወይም/እና በዓይነት ድጋፍ ሊፈቀድ ይችላል፤

፮. ኮሚሽኑ በከተማው ክልል ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎች ከአደጋ በፊት ለጊዜው የሚቆዩበት ማዕከል ግንባታና መሰረተ ልማት እንዲሁም ድጋፍ በከንቲባ ሲወሰን ፈንዱን መጠቀም ይችላል፡፡

፳፮. **የመልሶ ግንባታና በዘላቂነት መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ትግበራ ሂደቶች**

፩. ኮሚሽኑ

ሀ) የአደጋ ተጎጂዎችን በስነ-ልቦና፤ በቁሳዊና ቋሚ ሀብት ለመደገፍ ይለያል፣

ለ) በቂ የስነ-ልቦና ድጋፍ፣ ሳይንሳዊ የውድመት መጠንና አይነት ትንተና፣ የመልሶ ግንባታና በዘላቂነት ማቋቋም ፓኬጅ ይቀርጻል፤

4. Under the provision of Sub Article (2) of this Article, any aid that was studied at the time and not approved or recognized by the Commission could not be covered from funds;

5. A resource reserved for disaster reserves cannot be used for other support unless authorized by a Mayor without natural or man-made disaster.

25. **Emergency Fund-Use**

1. The fund's money will be used for emergency humanitarian support, restoration and sustainable rehabilitation of people who are victims of natural and man-made disasters;

2. Emergency funding will also be used in accordance with the package project proposal prepared by the Commission;

3. Where necessary, support may be provided to the relevant Federal Executive Institution or to the Regional States in accordance with the City Government's decision;

4. Those that can be covered with the aid of the fund will be for natural and man-made disasters that are prioritized by the Commission depending on the degree of risk;

5. Notwithstanding the provision of Sub Article (3) of this Article, it may be allowed with financial or/and in-kind support from the fund when decided by a Mayor;

6. The Commission can also use the fund when it is decided by a Mayor that the construction and infrastructure, as well as support, of a center where people at risk in the City region can stay temporarily before a disaster.

26. **Restoration and Sustainability Rehabilitation Project Implementation Processes**

1. The Commission

a) Identifies disaster victims psychologically; materially and to support permanent treasure;

b) Enough psychological support, scientific analysis of the extent and type of failure, designs a package of restoration and rehabilitate in sustainability;

ሐ) በተቀረጸው ፓኬጅ አማራጭ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ዝግጅት ያደርጋል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ጥናቶችን ያጠናል ወይም ያስጠናል፤ በጀት ይመድባል፣

፪. ኮሚሽኑ የመልሶ ግንባታና በዘላቂነት መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክቶችን ያስተገብራል፤ ይከታተላል፤ ይረከባል፤ ለተጎጂዎች እንዲተላለፉ ያደርጋል፡፡

**፳፯. <u>ከአደጋ ዝግጁነት ፈንድ ስለሚሰጡ ድጋፎች</u>**

ለአደጋ ተጎጂዎች የሚሰጥ ድጋፍ የሚከተሉት ናቸው፡-

፩. በአስቸኳይ ጊዜ ሰብዓዊ ዕርዳታ የሚሰጡ ድጋፎች፡-

ሀ) መሰረታዊ የምግብ ነክ ድጋፍ፣

ለ) የሌሊትና የቀን ልብስ፣

ሐ) መሰረታዊ የቤት ቁሳቁስ፣

መ) የሥነ-ልቦና እና ማረጋጋት ድጋፍ፣

ሠ) መሰረታዊ የንጽህና መጠበቂያ፣

ረ) መሰረታዊ የሆኑ ጊዜያዊ መጠለያና መሰረተ ልማት፤

፪. በመልሶ ግንባታ ፕሮጀክት ትግበራ የሚሰጡ ድጋፎች፡-

ሀ) ከጊዜያዊ ድጋፍ በኋላ የወደመ ንብረት ባለበት መልሶ መጠገንና መገንባት፣

ለ) የትምህርት ቁሳቁስና ክፍያ ድጋፍ፣

ሐ) የህክምና እና መድሃኒት ድጋፍ፣

መ) የመስሪያ ካፒታል ድጋፍ፣

ሠ) ልዩ ልዩ ስልጠናዎችና ቴክኒካል ድጋፎች፣

ረ) የመጠለያ ቤት ባለበት ሁኔታ መልሶ ግንባታ ወይም የቤት መስሪያ የገንዘብ ድጋፍ፣

ሰ) የቤት ግንባታ ቁሳቁስ ድጋፍ፤

፫. በዘላቂነት መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ትግበራ የሚሰጡ ድጋፎች፡-

ሀ) ፕሮጀክቱ እስከሚጠናቀቅ ጊዜያዊ መጠለያ የቤት ኪራይ ድጋፍ ፣

ለ) የሥራ ዕድልና ስልጠና እና የሥራ መስሪያ ካፒታል ድጋፍ፣

ሐ) ለሞት የቀብር ማስፈጸሚያ እና ቤተሰብ ሥነ-ልቦና ማጽናኛ ድጋፍ፣

c) With the modeled package, an alternative project proposal makes arrangements; it studies or studies additional studies as needed; it assigns a budget;

2. The Commission implements and monitors restoration and rehabilitate in sustainability projects, take over them, and make them available for transfer to victims.

**27. <u>Support Grants from the Disaster Readiness Fund</u>**

Support for disaster victims is as follows:

1. Grants for humanitarian aid urgently:
   a) Basic Food-related Support;
   b) Night and formal wear;
   c) Basic Home Material;
   d) Psychological and Stabilization Support;
   e) Basic Hygiene;
   f) Basic temporary accommodation and infrastructure.
2. Grants provided by the implementation of the restoration project:
   a) Repair and building where there was property destroyed after temporary support;
   b) Educational material and payment support;
   c) Medical and drug support;
   d) Work capital support;
   e) Miscellaneous training and technical grants;
   f) Restoration or homework funding in the presence of a shelter house;
   g) Home building material support.
3. Grants provided by the implementation of the sustainable restoration project:
   a) Temporary shelter rental support until the project is completed;
   b) Employment opportunity and training and work operative capital support;
   c) Support for death funeral enforcement and family psychological support;

መ) በቤተሰብ የሚደረግ መሰረታዊ ፍጆታ ድጋፍ፣

ሠ) የቤት ውስጥ ቁሳቁስና የአልባሳት ድጋፍ፣

ረ) የወደመ ቤትና ንብረት፣ መሰረተ ልማት በተሻለ ሁኔታ በዘላቂነት ባለበት ወይም በምትክ ቦታ መገንባት ወይም በሌሎች አማራጮች እንዲያገኙ በማድረግ ወጪውን መደገፍ፣

ሰ) ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የገቢ ምንጭ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ ሊያሳትፍ የሚያስችል ፕሮጀክቶች ማዘጋጀትና ወደ ሥራ እንዲገቡ መደገፍ ናቸው፡፡

፳፰. የድጋፍ አወሳሰንና መጠን

፩. የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፎች ለድንገተኛ አደጋ ተጎጂዎች የሚሆን እርዳታ ከኮሚሽኑ መጠባበቂያ መጋዘን ወጪ ሆኖ ይሰጣል፤

፪. የአሰቸኳይ ጊዜ፣ በመልሶ ግንባታና በዘላቂነት መልሶ ማቋቋም ድጋፎች በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ ስለሚደረገው ድጋፍ መጠን፣ ብዛትና የሰዎች ጥምርታ፣ ስታንዳርድ፣ ፓኬጅና የጊዜ ገደብ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

፫. በመልሶ ግንባታና በዘላቂነት መልሶ ማቋቋም ድጋፎች በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ድጋፎች ኮሚሽኑ በሚያዘጋጀው የፓኬጅ ማዕቀፎች ይሆናል፤

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳፱. የፈንዱ የባንክ ሂሣብ

የፈንዱ ገንዘብ በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮ በኮሚሽኑ ስም በሚከፍተው ልዩ የባንክ ሂሣብ ይቀመጣል፡፡

፴. የፈንዱ የሂሣብ ሰነዶች

፩. ኮሚሽኑ የፈንዱን ሂሣብ በሚመለከት የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪. የፈንዱ ሂሣብ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

d) Funding for basic consumption by family;

e) Home material and clothing support;

f) Support the cost by ensuring that destroyed housing and property, infrastructure are best built in a sustainable or replacement location, or that they are available with other options;

g) Are to develop projects that can engage with other stakeholders in jobs that provide a source of income, and to support them in getting to work.

28. **Support Determination and Quantity**

1. Emergency supports provide aid to emergency victims as a cost from the Commission's backup warehouse;
2. Emergency, restoration and sustainable rehabilitation grants are determined by the directive issued by the Commission on the amount, quantity of support in cash and kind, number of people in support and person's ratio, standard, package and time limit;
3. Support for restoration and sustainable rehabilitation, both in-kind and in-cash, will be provided through the package frameworks that the Commission develops.

## PART SIX

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

29. **Bank Accounts of the Fund**

The money of the fund will be deposited in a special bank account that will be opened by the City Government's Finance Bureau on behalf of the Commission.

30. **The Fund's Accounting Documents**

1. The Commission holds complete and accurate balance sheets regarding the fund's accounts;
2. The fund's account is examined annually by the General Auditor or the Auditor who designates it.

፴፩. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ለአደጋ ዝግጁነት ፈንድ ሥራ ታስቦ የተሰበሰበና በሥራ ላይ ሳይውል የቀረ ገንዘብ እና ንብረት በዚህ ደንብ ወደ ፈንዱ ይዘዋወራል፡፡

፴፪. **የመተባበር ግዴታ እና ኃላፊነት**

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፴፫. **ስለ ተጠያቂነት**

ማንኛውም ሰው ከዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ውጭ የሰራ ወይም ደንቡ በአግባቡ እንዳይፈፀም ያሰናከለ ወይም ለተቋቋሚዎች የሚሰጠውን ገንዘብ ለግል ጥቅሙ ያዋለ አግባብነት ባላቸው የፍትሐብሔር ወይም/እና በወንጀል ወይም/እና በአስተዳደር ሕጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፴፬. **ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው አሰራሮች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ካቢኔው ያወጣው ደንብ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፴፭. **መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

ኮሚሽኑ ይህን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፴፮. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከመጋቢት መጋቢት ፴ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት መጋቢት ፴ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ/ም**

**አዳነች አበቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

31. **Transitory Provisions**

Prior to the coming into force of this Regulation, money and property collected and left in force for the work of the disaster readiness fund will be transferred to the fund under this Regulation.

32. **Duty to Co-operation and Responsibility**

Anyone has the duty to cooperate in the enforcement of this Regulation.

33. **Liability**

Any person who has worked outside the provisions of this Regulation or disables the Regulation from being properly enforced, or who has invested funds to the settlements for their own use, shall be liable under relevant Civil or/and Criminal or/and Administrative Laws.

34. **Inapplicable Procedures**

Any regulation or customary practice issued by the Cabinet that contravenes this regulation shall not apply to matters covered by this regulation.

35. **Power to Issue Directives**

The Commission may issue directive to enforce this regulation.

36. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of April 8, 2025.

**Done at Addis Ababa, this 8th day of April, 2025.**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**